# ልዩ መልእክት

## ይድረስ፡
## ለኪዳናውያንና ለኪዳናውያት
## የኢትዮጵያ ልጆች!

---

**ለእግዚአብሔር፡ መንግሥቱ፥**
**ለእናንተም፡ እናት አገራችሁ ኢትዮጵያ ለኾነችው**
**ድንግል ማርያም፡**
**እውነተኞችና ታማኞች ልጆች ለኾናችሁት፥**
**በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖታችሁና ምግባራችሁ**
**ጸንታችሁ ለምትኖሩ፥**
**ደግሞም፡ እየራሳችሁን፡ በንስሓና በገድል፡**
**ለዚሁ ታላቅ የሕይወት ጸጋ ላበቃችሁትና**
**ለማብቃት ለምትጋደሉ: አዎን! ለእናንተ ኹሉ!**

---

**የእግዚአብሔር ሰላምታችን ይድረሳችሁ!**

ኢትዮጵያዊው ቅዱስ ዲዮስቆሮስ፡ በመንፈስ ቅዱስ ተመልቶ በደረሰው ቅዳሴያችን፡ "ከመ እንተ ብእሲ ለጸዊም፡ በውስተ ገዳም ኀደረ፤ እምኀበ ዲያብሎስ ተመከረ፤ በኃይለ መለኮቱ፡ መኳንንተ ጽልመት ሠዐረ።"

ማለትም፡ "ሰው በኾነበት ትስብእቱ ለመጾም፡ ለብቻው፡ ወደበረሃ ገባ፤ በዚያም ሣለ፡ ከዲያብሎስ በቀረበለት ገድል ተፈተነ፤ በአምላክነቱም ኃይል፡ የጨለማን ሥልጣናት ሻረ!" ብሎ የተናገረለትን፡ የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ጾም፡ እነሆ ልንጀምረው ተዘጋጅተናል። እርሱም፡ ‹ዓቢይ ጾም›፥ ወይም፡ ‹ታላቁ ጦም›፥ ወይም፡ በሕዝባዊ አነጋገር፡ ‹ሑዳዴ› የምንለው ነው።

የዛሬው መልእክታችን፡ እንደተጋዳይ ዐርበኛ፡ ወደመስቀሉ ሰልፍ የሚገሠግሠው፡ መሢሑ ኢየሱስ፡ የጫጉላውን እልፍኝ በሚናፍቅ ሙሽራ ተመስሎና "መርዓዊ" ተብሎ በተሠየመበት ሳምንት ውስጥ የቀረበው ያለምክንያት አይደለም፤ መጪው ወራት፡ የጌታ ጾምና ፈተናው የሚዘከርበት ብቻ ሳይኾን፡ ከእኛ፡ ከቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ሕይወት ጋር ያለውን የተሣሠረ ውሕደት ጭምር፡ በትክክል ተገንዝበን፡ ከእያንዳንዳችን የሚፈለግብንን የገድል ግዳጅ ለመፈጸም እንድንችል ይረዳን ዘንድ፡ ታስቦበት ነው። ስለዚህ፡ በአንክሮና በተዘክሮ፥ በትኵረትና በተመስጦ ልትመለከቱትና ልታስተውሉት እንደሚገባ፡ አስቀድመን ልናሳስባችሁ እንወድዳለን።

ለመግቢያ ያህል፡ ይህን ካልን፡ ከጌታ ጾምና ፈተናው ጋር የተሣሠረ ውሕደት ስላለው፡ ስለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታችን ጤናማ ህልውናና የሚያስተማምን ጥበቃ፡ ሊነግረን ወደቀረበው፡ ወደዚህ መልእክት ፍሬ ነገር እንውሰዳችሁ!

አዎን! የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነትን፡ ጠብቆና አጽንቶ መኖር ማለት፡ እነሆ ዛሬ፡ የ፯ሺ፭፻፭ (ሰባት ሽህ አምስት መቶ አምስት) ዓመታት ዕድሜ ያለውን፡ እውነተኛውን የተዋሕዶ ሃይማኖት፡ በእውነት መንፈስ ተቀብሎና በትክክለኛው የበጎ ምግባር አምልኮ፡ ፈጽሞ መገኘት ማለት ነው። ይህም፡ "የአንድ ሰብአዊ ፍጡር ነፍስ፡ በሥጋዊውና በመንፈሳዊው ኹለንተናዋ፡ የትንሣኤንና የሰንበትን መልካም የአገልግሎትና የዕረፍት ሕይወት፡ ዛሬም፥ ዘወትርም፥ ለዘለዓለምም ለመኖር የሚያበቃትን፡ የመጨረሻውን የአሸናፊነት የድል አክሊል መቀዳጀት" ነው።

ይህ ታላቅ ቍም-ነገር፡ ሰፊ ትንተናና ረዥም ሓተታ እንደሚያሻው አያጠያይቅም፤ ይኹን እንጂ፡ ይህን አርእስተ ጉዳይ፡ ማለትም፡ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን፥ ኢትዮጵያዊዉንና ኢትዮጵያዊቷን በሚመለከት፡ እኔ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያ አገልጋይ፡ ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ፡ ቀደም አድርጌ፡ አዘጋጅቼ ባቀረብሁላችሁ መጻሕፍት፡ በሚበቃ ስለተብራራላችሁ፡ ተረድታችሁታልና፡ እዚህ ላይ፡ ተጨማሪ ገለጣ የሚያስፈልጋችሁ አይመስለንም።

ስለዚህ፥ ይኸው ታላቅ ቍም-ነገር፡ አኹን በተነሣንበት ዓላማ አኳያ፥ ባጭር ቃል ተጠቃልሎ ሲገለጽ፡ "**የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነትን፡ ጠብቆና አጽንቶ መኖር**" ማለት፡ "**ለወንዶቹ፡ ኢየሱስ ክርስቶስን፥ ለሴቶቹ ደግሞ፡ ድንግል ማርያምን መስሎ መገኘት ነው።**" ያም፡ "እነርሱ የኾኑትን፡ እኛም መኾን ይገባናል! በእነርሱ ላይ የደረሰው ኹሉ፡ በእኛም፡ በእያንዳንዳችን ላይ ሊደርስብን ይችላል!" ብሎ በማመን፡ የእነርሱን ጽዋ፡ በፍጹም ፈቃደኛነትና ቈራጥነት መካፈል ነው።

ከዚህ የተነሣ፡-

<u>በመጀመሪያ፡</u> ይህን፡ የቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖታችሁን፡ አውቃችሁትና ተቀብላችሁት፡ በምግባር እየኖራችሁት የምትገኙት እናንተ፡ ኪዳናውያን ኢትዮጵያውያንና ኪዳናውያት ኢትዮጵያውያት፡ እያንዳንዳችሁ፡ በየስማችሁ፡ በመንፈስ ቅዱስ እጅ፡ በሕይወት መጽሓፍ፡ በቀዳሚነት፡ እንደተመዘገባችሁ ማረጋገጣችሁን አምናችኋል።

<u>በመቀጠል፡</u> ይህ መለኮታዊ እውነታ መኖሩን ባለማወቅ፥ አለዚያም፡ አውቀውት፥ ነገር ግን፡ ከፈጣሪያቸው በላይ፡ የበለጠ ያወቁ መስሏቸው፡ በመሳሳት፥ ይልቁንም፡ ከጥንት ጀምሮ፡ ይህችን የእግዚአብሔርን እውነት፡ በሓሰት ለውጦ ለመተካት በመሞከር፡ አዳምንና ሔዋንን፡ ከፈጣሪያቸው ከእግዚአብሔር የለያቸው፡ "እባብ፥ ዘንዶ፥ ዲያብሎስ፣ ሰይጣን፥ ርኩስ መንፈስ፥ ጋኔን" እየተባለ፥ በሌላውም የጣዖትና ባዕድ አምልኮ እየተመሰለ፡ በመላው ዓለም የገነነው የክፋት ኃይል፡ ሲያካኼድ በኖረው የጥፋት ወጥመዱ በመጠለፍ፥ ወይም፡ በምርጫቸው፡ የእርሱ መሣሪያዎች ኾነው በሚያገለግሉት ሰብአውያን ፍጡራን ተንኰል በመታለል እየጠፉ እንደሚያልቁት ደካሞች፡ ተማርካችሁ፡ ከተወሰዳችሁበትና ከወደቃችሁበት ያላዋቂነት ዐዘቅት፡ እየራሳችሁን በንስሓ አእምሮ አድሳችሁ በመመለሳችሁ፡ "ንዑ ኀቤየ! ቡሩካኑ ለአቡየ!" ማለትም፡ "አባቴ የባረካችሁ፡ እናንተ! ወደእኔ ኑ!" በሚለው አምላካዊ አቀባበል፡ ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት የበቃችሁት፡ ወንዶችና ሴቶች፡ እናንተም፡ በዚህ የገድል ሙያችሁ፡ በአምላካዊው ቃል ተሞግሳችሁ፡ እያንዳንዳችሁ፡ በየስማችሁ፡ በመንፈስ ቅዱስ፡ በሕይወት መጽሓፍ እንደተመዘገባችሁ አውቃችኋል።

__በመጨረሻም፡__ ለዚህ፡ ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ሕይወት፡ እየራሳችሁን፡ ገና ያላበቃችሁ፥ ነገር ግን፡ እውነተኛ ምንነቱን፡ በጤናማው ሃይማኖታዊ ሰውነታችሁ፡ ከሩቅ ተመልክታችሁ፥ ጣፋጭ መዓዛውንም፡ ከሩቅ አሽትታችሁ፡ በእውን ትኖሩት ዘንድ፡ እነሆ፡ በጠባቡ የገድል ጎዳና ላይ፡ እየገሠገሣችሁ፡ ልትደርሱበትና ልትገቡበት፡ ወደምትጣደፉበት፡ ወደጠባቡ ደጃፍ የምትዃዙም ኹሉ፡ የድሉን አክሊል ሊቀዳጅ እንደተቃረበ ጐበዝ ዐርበኛ፡ ሩጫችሁን ፈጽማችሁ፡ እናንተም፡ እያንዳንዳችሁ፡ በየስማችሁ፡ በመንፈስ ቅዱስ፡ በሕይወት መጽሓፍ ትመዘገቡ ዘንድ፡ እነሆ፡ በያላችሁበት እየተጠበቃችሁ መኾናችሁን ተገንዝባችኋል።

ባጠቃላይ ኹላችሁም፡ ይህን የቅዱሱን ኪዳን ኢትዮጵያዊነት፡ ለ፯ሺ፭፻፭ (ሰባት ሽህ አምስት መቶ አምስት) ዓመታት አቆይተው፡ ዛሬ፡ ለእኛ ያስረከቡን የቀደሙት ኪዳናውያን አባቶቻችንና ኪዳናውያት እናቶቻችን፡ ይህን ለማድረግ የቻሉት፡ በእንዴት ያለ፡ የእምነትና የምግባር ገድልና ጽናት መኾኑን፥ ምን ዓይነቱንና የቱን ያህል ከባድ የኾነውንም መሥዋዕትነት በመክፈል መኾኑን፡ እዚህ ላይ፡ ለእናንተ፡ እንደገና ማውሳትና ማተት የሚያስፈልገን አይኾንም።

ከፈጣሪያቸው ጋር፡ የሰባቱ ቃል ኪዳናት ተዋዋዮች የኾኑትን፡ ቅዱሳን ወንዶችና ቅዱሳት ሴቶች፥ የእነርሱንም ፈለግ ተከትለው፡ ለድል አድራጊነቱ አክሊል የበቁትን፡ የቀሩትን፡ የነቢያትንና የሓዋርያትን፥ የጻድቃንንና የሰማዕታትን ዜና ሕይወታቸውን፡ ጥሩ አድርጋችሁ ስለምታውቁት፡ አዎን! ሌላ ተጨማሪ ሓተታ አያስፈልጋችሁም።

ለአብነት ግን፡ የዘለዓለም ሕይወትን፡ ለፍጥረተ ዓለሙ ያስገኙትን፡ የፈጣሪያችንን፡ የኢየሱስ ክርስቶስንና የቅድስት እናቱን፡ የድንግል ማርያምን የምሕረት ቃል ኪዳን፡ ለዝክረ ነገር አንሥተን፡ እዚህ ላይ መጥቀሱ ይበቃናል። ያም፡ የእምነታችሁ እውቀት፡ አካል በመኾኑ፡ አንዘረዝረውም።

እንግዴህ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነትን ጠብቆና አጽንቶ ለማቆየት፥ በህልውናውም እንዲቀጥል ለማድረግ፡ እንደመሪዎቻችንም ባይኾን፡ ለዚያ ግዳጅ የሚመጥን፡ ገድላዊ መሥዋዕትነትን መክፈል፥ ወይም፡ ለመክፈል፡ ራስን ማዘጋጀት፡ ከእያንዳንዳችን፡ እንደሚጠበቅብን፡ ይኸው የምንኖርበት የሃይማኖታችን እውቀት፡ ዘወትር ያስታውሰናል።

ይህም ቢኾን፡ "በመሪዎቻችን ላይ ደርሶና ተፈጽሞ እንደታየው፡ እስከዚያ የሚያበቃ፡ የገድልና የመሥዋዕትነት ድርሻ፡ ከእያንዳንዳችን ይጠበቅብናል!" ማለት አይደለም፤ እርሱ፡ ራሱ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ **‹ወበዓለምሰ ሀለወክሙ፡ ሕማመ ትርከቡ፤ ወባሕቱ ጽንዑ! እስመ አነ ሞዕክዎ ለዓለም።› ማለትም፡ ‹በዓለም ሣላችሁ፡ በመከራ መፈተናችሁ አይቀርም። ነገር ግን፡ አይዟችሁ! እኔ፡ ዓለምን አሸንፌዋለሁና፡ እናንተም፡ የሚመጣባችሁን መከራችሁን ኹሉ፡ ስለምታሸንፉት፡ እስከመጨረሻው ጸንታችሁ ተቋቋሙት እንጂ፡ አትፍሩት!›** ብሎ የሰጠን መመሪያ ቃል፡ ምንጊዜም ትዝ ሊለን ይገባል። (ዮሐ. ፲፮፥ ፴፫።)

እንዲህ ከኾነ፡ በመጀመሪያ ነገር፡ መከራው ላይገጥመን ይችላል፤ ምናልባት ግን፡ በመታደል፡ የሚገጥመን ቢኾን እንኳ፡ ያን መከራ፡ እርሱ መሪያችን ኢየሱስ ክርስቶስ፥ ቅድስት እናቱ ድንግል ማርያምም፡ ከእኛ አስቀድመው፡ ተሸክመውና ተቋቍመው ስላሸነፉልንና ስላስወገዱልን፡ በእነርሱ ቤዛነት፡ ከተቀዳጀነው፡ ከመንፈስ ቅዱስ ጸጋ የተነሣ፡ እኛን፡ መከራው የማያገኘን፥ ቢደርስብንም፡ የማይስሰማን፥ እንዲያውም፡ በደስታ ተቀብለንና ተቋቍመን፡ ድል የምንነሣው እንኾናለን።

ለዚህ እውነታ ማረጋገጫ፡ በቅርቡ የኾነውን፡ ከዘመናችን ዜና መዋዕል አንዱን ብቻ፡ ለዓይነት፡ በማስረጃነት ማቅረብ ይቻላል፤ ይኸውም፡ ኢትዮጵያዊው ሰማዕት፡ ቅዱስ ጴጥሮስና እርሳቸውን የመሰሉት፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ በመሥዋዕትነታቸው፡ ከአምስት ዓመታት መከራ በኋላ፡ በግፈኛው ፋሺስት ጣልያን ወራሪ ጦር ኃይል ላይ የተቀዳጁት የነጻነት ድል ነው።

ከዚህ በመለስና ከዚህ ይልቅ፡ ሊያሳስበን የሚገባው፡ በዚህ ረገድ፡ በእኛ፡ በኪዳናውያንና በኪዳናውያት ላይ የሚደርስብን፡ የማይቀረው የፈተናና የመከራ ጽዋ ነው፤ እርሱም፡ ከየራሳችን ውስጥና ከቤተሰባችን እየመነጨ፡ ሊያዳክመንና ሊያጠቃን፥ ከዚያም ሊያሸንፈን የሚቃጣው፡ ተፃራሪ ኃይል ነው። ይህም፡ **‹ወሰብእ ቤቱ፡ ይፃረሮ ለሰብእ!›** ማለትም፡ **‹ለሰው፡ [ለወንዱም፥ ለሴቱም፡] የራሱ ቤተሰብ፡ ጠላት ይኾነዋል!›** የሚለው፡ የመሪያችን አምላካዊ ቃል ኾኖ ይገኛል። (ማቴ.፲፥ ፴፮።)

ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖታችንና ምግባራችን፡ አማናውያንና ሕያዋን አብነቶቻችን የኾኑትን፡ ኢየሱስ ክርስቶስንና ድንግል ማርያምን መከተልንና እነርሱን መምሰልን፡ በእውነት ፈልገንና በቍርጥ ወስነን ለመረጥነው፡ ለእውነተኞቹ ኪዳናውያንና ኪዳናውያት የኢትዮጵያ ወንዶችና ሴቶች ልጆች፡ "ቀዳሚውና መሠረታዊው፥ ከባዱና የተለየ ኾኖ፡ ከፊታችን የሚደቀነው ፈተናና መከራ ምን ይኾን?" ብለን ለማወቅ ብንሻ፡ አዎን! ትክክለኛ መልሱን፡ በእርግጥ የምናገኘው፡ ከዚሁ፡ ከማይታበለው፡ ከመለኮታዊው የመሪያችን ቃል መኾኑን እናረጋግጣለን። ያም፡ "<u>ከየራሳችን ቤተሰብ የሚነሣሣብን፡ ብርቱ ተቃውሞ ነው!"</u> የሚለው ነው።

ይህን መመሪያውን፡ መምህራችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ እንዲህ ሲል አብራርቶልናል፡- ‹ኵሉ፡ ዘየአምን ብየ በቅድመ ሰብእ፡ አነሂ አአምኖ፡ በቅድመ አቡየ ዘበሰማያት። ወለዘሰ ክሕደኒ በቅድመ ሰብእ፡ አነሂ እክሕዶ፡ በቅድመ አቡየ ዘበሰማያት።

‹ኢይምሰልክሙ፡ ዘአምጻእኩ ሰላመ ለምድር፤ አላ መጥባሕተ። ዘያፈቅር አባሁ፥ ወእሞ፥ ወብእሲቶ፥ ወቤቶ፥ ወውሉዶ፥ ወአኀዊሁ፥ ወአኃቲሁ፥ ወዓዲ ነፍሶሂ እምኔየ፡ ኢይክል ከዊነ ረድእየ። ወኢያጥብዐ፥ ወዘኢነሥአ መስቀለ ሞቱ፥ ወዘኢተለወ ድኅሬየ፡ ኢይደሉ ሊተ፤ ወኢይክል ይጸመደኒ። ዘረከባ ለነፍሱ፡ ለይግድፉ! ወዘሰ ገደፉ ለነፍሱ በእንቲአየ፡ ይረክባ።›

ማለትም፡ ‹በእኔ የሚያምን መኾኑን፡ በሰው ፊት ለሚመሰክርልኝ ኹሉ፡ እኔም፡ ስለዚህ እምነቱ፡ በሰማዩ አባቴ ፊት፡ እመሰክርለታለሁ። በእኔ የሚያምን መኾኑን፡ በሰው ፊት የሚክደውን ግን፡ እኔም፡ ስለዚህ ክሕደቱ፡ በሰማዩ አባቴ ፊት፡ እመሰክርበታለሁ።

‹በምድር ላይ፡ የሚለያይ ሰይፍን እንጂ፡ [የግብዝነትን አስመሳይ] ሰላምን ለማምጣት የመጣሁ አይምሰላችሁ! [መለያውም ሰይፍ፡] አባትን፥ እናትን፥ ሚስትን፥ [ባልን]፥ ወንዶችና ሴቶች ልጆችን፥ ወንድሞችንና እኅቶችን፥ ቤትን [ትዳር ንብረትን]፥ ራስንም እንኳ ሳይቀር፡ ከእኔ አብልጦ የሚወድድ፡ ለእኔ፡ አገልጋዬ ሊኾን የማይችል መኾኑ ነው። እስከሞት የሚያደርሰውን፡ የመከራ መስቀሉን ተሸክሞ ሊከተለኝ ጨክኖ ያልተነሣ፡ ለእኔ ሊኾን አይገባም፤ ሊያገለግለኝም አይችልም።

‹'ራሴን አድናለሁ!' የሚል፡ ነፍሱን ያጠፋታል፤ ራሱን፡ ስለእኔ የሚሠዋ ግን፡ ያድናታል።› (ማቴ.፲፥ ፴፪-፴፱። ሉቃ. ፲፬፥ ፳፮-፳፯።)

በዚህ ጥቅስ ውስጥ፡ ባለምሥራቹ ማቴዎስ፡ ‹ዘያፈቅር...እምኔየ› ማለትም፡ ‹ከእኔ ይልቅ፡ [ሌላውን አብልጦ] የሚወድድ› ያለውን መለኮታዊ ቃል፡ ባለምሥራቹ ሉቃስ፡ ‹ለእመ ኢጸልአ› ማለትም፡ ‹[ሌላውን] ባይጠላ› በሚል ጠንካራ ቃል፡ መልእክቱን፡ ያከበደው መኾኑ፡ በአጽንዖት ሊጤን ይገባል፣ ያስፈልጋልም።

ይህንኑ የመለኮታዊ መሪያችንን መመሪያ ቃል፡ እስኪ ጠለቅ ብለን እንመልከተው! ልብ አድርገንም እናስተውለው!

<u>አንደኛ.</u> መለኮታዊ ሰይፍ የኾነው፡ ይህ፡ የመመሪያው ቃል አፈጻጸም የሚጀምረው እኮ፡ በቅድሚያ፡ ከየራሳችን ነው፤ ይህም፡ ‹ወዓዲ ዘያፈቅር ነፍሶሂ እምኔየ› ወይም፡ ‹ለእመ ኢጸልአ ነፍሶ!› ማለትም፡ ‹ከእኔ ይልቅ ራሱን የሚወድድ›፥ ወይም፡ ‹ራሱን ባይጠላ› ስላለ ነው። በዚህ ረገድ፡ለእየራሳችን፡ የመጀመሪያው ጠላት፡ "እየራሳችን ነን!" ማለት ነው።

ይኸውም፡ በምሥጢረ ተዋሕዶ፡ አንድ የኾኑት፡ ሦስቱ፡ የነፍስ፥ የሥጋና የመንፈስ አካላትና ባሕርያት፡ በተለያዩት አካሎቻቸውና ባሕርዮቻቸው ምክንያት፡ አንዳቸው ለአንዳቸው ፈተና እየኾኑ ስለሚቀርቡ፡ ጠላትነቱና ገድሉ፡ ከዚያ ይጀምራል።

በአንድ ሰብአዊ ፍጡር ሰውነት ውስጥ፡ ጠላትነቱና ፈተናው እጅግ ዐይሎ፡ "ገድል" የሚባለው ትግሉና ጦርነቱ የሚጸናው፡ የዚያ ሰብአዊ ፍጡር ነፍስ፡ ራስዋ ከምትፈጥረው፥ ወይም፡ የአካባቢዋ ተፅዕኖ ከሚያስከትልባት፡ የፍላጎት ዝንባሌዋና የፈቃድ ውሳኔዋ የተነሣ፡ ምርጫዋ፡ ከመንፈሳዊው ይልቅ፡ ወደሥጋዊው የሚያመዝን ኾኖ ሲገኝ መኾኑ፡ በእናንተ ዘንድ የሚታወቅ ግልጽ እውነታ ነው።

መምሕራችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ‹መንፈስ ውእቱ ዘየሐዩ፤ ወሥጋሰ፡ አልቦ ዘይበቍዕ፣ ወኢምንተኒ፤ ወዝኒ ቃል፡ ዘአነ ነገርኩክሙ፡ መንፈስ ውእቱ፤ ወሕይወት ውእቱ።" ማለትም፡ ‹ሕይወትን የሚሰጥ፡ መንፈስ ነው። ሥጋ፡ ምንም አይጠቅምም። ይህም፡ እኔ የነገርኋችሁ ቃል፡ መንፈስ ነው፤ ሕይወትም ነው።" ብሎ የተናገረውን መሠረት አድርጎ፡ ባለምሥራቹ ሐዋርያ፡ እንዲህ ሲል የጻፈው መልእክቱ፡ ይህን ኹኔታ ያረጋግጣል።

‹እስመ ኵሎሙ፡ እለ ለግዕዘ ነፍስቶሙ ይገብሩ፡ ዘዝንቱ ዓለም ይሔልዩ፤ ወእለሰ ዘመንፈስ፡ ይሔልዩ ዘመንፈስ። ወሕሊናሁሰ ለነፍስትነ፡ ሞተ ያመጽእ ላዕሌነ፤ ወሕሊናሁሰ ለመንፈስ፡ ሰላመ፥ ወሕይወተ፡ ይሁበነ። እስመ ሕሊናሁ ለነፍስትነ፡ ፀሩ ለእግዚአብሔር ውእቱ፤ እስመ ኢይገርር ለሕገ እግዚአብሔር፤ ወኢሂ ይክሎ። እስመ ኵሎሙ፡ ለግዕዘ ነፍስትክሙ ይገብሩ፡ ለእግዚአብሔር አድልዎ ኢይክሉ።›

ማለትም፡ ‹ለሥጋቸው ጠባይ የሚስማማውን የሚሠሩ ኹሉ፡ የዚህን ዓለም ነገር ያስባሉ፤ እንደመንፈስ ፈቃድ የሚኖሩ ግን፡ የመንፈስን ነገር ያስባሉ። የሥጋችን አሳብ፡ ሞትን ያመጣብናል፤የመንፈስ አሳብ ግን፡ ሰላምንና ሕይወትን ይሰጠናል። የሥጋችን አሳብ፡ ለእግዚአብሔር፡ ጠላቱ ነውና፤ ለእግዚአብሔር ሕግ አይገዛምና፤ መገዛትም ተስኖታል። ለሥጋዊ ፈቃዳቸው የሚገዙ ኹሉ፡ እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይችሉምና። (ዮሓ. ፮፥ ፷፫። ሮሜ. ፰፥ ፭-፰።)

ስለዚህ፡ እያንዳንዳችን፡ እየራሳችን፡ የየቤተሰባችን፡ አንዱ አባል በመኾናችን፡ "ለሰው፡ ቤተሰቡ፡ ጠላት ይኾነዋል!" የሚለው መለኮታዊ ቃል፡ መነሻው አድርጎ ተፈጻሚነትን፡ ከየራሳችን ይጀምራል ያሰኘው፡ ምክንያቱ ይህ ነው፤ እውነታው ይህ ከኾነ፡ ይህንኑ ተገንዝበን፡ ከኹሉ አስቀድሞ፡ እየራሳችን፡ በራሳችን ላይ ያለውን ጠላትነት በዚህ፡ መለኮታዊ ሰይፍ በኾነው፡ መመሪያ ቃሉ ለይተን፡ ጠንቁን ማስወገድ ይኖርብናል።

ይህም የሚኾነው፡ ነፍሳችን፡ በቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖቷ ጸንታ፡ የሓሰትና የክፋት ዝንባሌ ያለውን፡ ግዙፍ ሥጋዋን፡ በጾምና በጸሎት፥ በስግደትና በምጽዋት የምግባር ኃይላቷ፡ ካጥፊነት ግፊቱ ገትታና አካኼዱን ተቆጣጥራ፡ የእውነትና የደግነት ንጽሓ ባሕርይ ላለው፡ ለረቂቅ መንፈሷ ፈቃድ እንዲገዛ ለማድረግ ስትችል ነው።

አዎን! ይህ የሚኾነው፡ ነፍስ፡ በምሥጢረ ሥላሴ መልክና በጥንተ ተፈጥሮ ሥርዓት፡ በተዋሕዶ፡ አንድ ኾነው እንዲኖሩ የተሰጧትን፡ ሥጋንና መንፈስን፡ ከራሷ አካልና ባሕርይ ጋር አስማምታ ስትገኝ ነው።

ኹለተኛ. ከየራሳችን በኋላ የሚከተለው፡ ኹለተኛው ጠላትነት የሚመነጨው ደግሞ፡ የቤተሰቡ ምሰሶዎች ከኾኑት፡ ከባል እና/ወይም፡ ከሚስት ነው። ይህም፡ በቤተሰቡ ውስጥ፡ ለሰው፡ ከየራሱ ቀጥሎ የሚነሣበት ጠላቱ፡ "ለወንዱ፡ ሚስቱ ትኾናለች፤ ለሴቷም፡ ባሏ ይኾናል!" ማለት ነው።

ስለዚህ፡ የቅዱሱ ኪዳን ባልና ሚስት፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በአዲስ ኪዳን ቃሉ፡ ‹ብእሴ ወብእሲተ፡ ኢኮኑ ክልኤተ፤ አላ፡ አሓዱ ሥጋ እሙንቱ። ዘእግዚአብሔር አስተጻመረ፡ ሰብእ ኢይፍልጥ!› ማለትም፡ ‹ባልና ሚስት፡ ኹለት አይደሉም፤ አንድ አካል ናቸው እንጂ። እግዚአብሔር፡ እንዲህ፡ አንድ ያደረገውን፡ ሰው አይለየው!" ባለው መሠረት፡ አንድ አካል ናቸው።

እንዲህ ይኹኑ እንጂ፡ ምናልባት፡ እንደዓለማውያኑ፡ በመካከላቸው ልዩነት ቢፈጠርባቸው፡ ከላይ በተጠቀሰው፡ በመለኮታዊው መመሪያ ሰይፍ ቃል፡ በእየራሳቸው ነፍስ፥ ሥጋና መንፈስ ላይ እንዳደረጉት ኹሉ፡ እንዲሁ፡ በመካከላቸው የተነሣውን፡ ያን ልዩነታቸውን፡ ጨርሰው አጥፍተውና አስወግደው፡ የቅዱሱ ኪዳን ሕይወታቸውን፡ በፍጹም ስምምነት መቀጠል ይኖርባቸዋል።

ሦስተኛ. እኒህ ባልና ሚስት፡ ወላጆች ኾነው፡ የቤተሰቡ ቍጥር፡ በልጆች እያደገ ሲኼድ፡ የዚያ ቤተሰብ አበቤት በኾነው አባት እና/ወይም፡ እመቤት በኾነችው እናት እና/ወይም፡ በኹለቱም ወላጆች እና/ወይም፡ በልጆች፥ ከዚያም፡ በወንድም እና/ወይም በእኅት፡ በተናጠልም ኾነ፡ በኅብረት፡ በሦስተኛ ደረጃ፡ አንዱ በአንዱ፥ ወይም፡ አንዱ፡ በኹሉም፥ ወይም፡ ኹሉም፡ በአንዱ፡ በጠላትነት የሚነሣሡ ይኾናሉ።

በዚህ ጊዜ፡ በእነዚህ የቤተሰብ አባሎች መካከል ለሚፈጠረው፡ ይህን ለመሰለው የእርስ በርስ መለያየት፡ መፍትሔው፡ ለባልና ሚስቱ እንደኾነው ኹሉ፡ ያው፡ ከላይ የተጠቀሰው፡ የመምህራችን መለኮታዊ መመሪያና የቅዱሳት መጻሕፍቱ ቃል፡ በእያንዳንዱ አባል፡ የሃይማኖትና የምግባር ቀራጥነት፡ በሥራ ላይ እንዲውል ሲደረግ ብቻ ነው።

<u>አራተኛ.</u> ይህ ኹኔታ፡ እንዲህ እያለ፡ ከቤተሰብ አልፎ፡ ወደቤተ ዘመድና ወደጓደኛ፥ ወደጎረቤትና ወደወዳጅ፥ ከዚያም፡ ወደኅብረተሰብና ወደአገር እየተስፋፋ ሊኼድ ይችላል። ነገር ግን፡ የኹሉም መነሻ ምክንያቱ፥ መንደርደሪያ ዓላማውና መድረሻ ግቡ፡ ያው አንድ ነው። ፈተናውና ጠላትነቱ፥ ጦርነቱና ገድሉም፥ በመጨረሻም፡ መፍትሔው፡ ያው፡ ከላይ እንደተብራራው፡ በየግል ሰውነት ላይ ከሚካኼደው፡ የተለየ አይደለም። አንድ ዓይነት ነው።

\+ \+ \+

አዎን! ቀደም ባለው፡ በጥንቱ የብሉዩ ዘመን፡ እግዚአብሔር፡ **"ከዘመዶችህና ከወገኖችህ [ከአገርህ] ተለይተህ ውጣ! እኔ ወደምመራህም ኺድ!"** ብሎ፡ በተናገረው ጊዜ፡ አብርሃም፥ ሣራም ጭምር፡ የፈጣሪያቸውን ጽኑ ቃል፡ ያለማወላወልና ያለማመንታት፡ እንዴት ባለ የጭካኔ ቈራጥ ውሳኔ፡ በሃይማኖት ተቀብለው፡ በምግባር እንደፈጸሙት፡ ከዚህ፡ ከአዲስ ኪዳኑ መመሪያ ጋር በማስተዋልና በማመዛዘን መመልከቱ፡ በተለይ፡ ለእኛ፡ አግባብ ይኾንልናል።

ምክንያቱም፡ ይኸው መመሪያ ቃል፡ ዛሬ፡ ለእኛ፡ ለእያንዳንዳችን፡ በነፍስ ወከፍ፡ ቀደም ብሎ፡ ከፊታችን ስለቀረበልን፣ አኹንም እየቀረበልን ስለኾነና ወደፊትም፡ መቅረቡ ስለማይቀር፡ ኹሉንም ዓይነት ጽዋ፡ እንዴት ልናስተናግደው እንደሚገባን አውቀን፡ ልንዘጋጅበት ስለሚያስፈልገን ነው። (ዘፍጥ. ፲፪፥ ፩-፫።)

ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከቅድስት እናቱ ጋር፡ በምድር ላይ እየተመላለሰ ሣለ፡ አምነውበት ከተከሉትና ዐብረውት ከነበሩት መካከል ሳይቀር፡ የዘለዓለም ሕይወት በኾነው፡ በእርሱና የዘለዓለም ሞት በኾነው በዓለሙ መካከል፡ ምርጫ ያደርጉ ዘንድ፡ ፈተና በሚቀርብላቸው ጊዜ፡ ዝንባሌያቸው፡ ወደየትኛው አግጣጫ ያጋደለ እንደነበረ፡ በገሃድ ታይቷል።

እርሱ፡ የአብ ቃል የኾነው መሪያችን፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በሰውነት ተገልጦ ሊሠዋላትና ቤዛ ኾኖ ሊታደጋት የመጣላትን፡ የእግዚአብሔርን መንግሥት መቀበሉ፡ ጭንቅ እየኾነባቸው፡ ከደቀ መዛሙርቱ መካከል ሳይቀር፡ ብዙዎች፡ ከእርሱ እየተለዩ፡ ወደኋላቸው ይመለሱ እንደነበረ፡ የዚያ ጊዜው ድርጊታቸው ይመሰክራል።

እንዲያ የኾኑት፡ ያለምክንያት አልነበረም፤ የዓለሙን ክብርና ሥጋዊ ጥቅሙን ሲያጡ፡ ሊደርስባቸው የሚችለውን ችግር ከመፍራት፥ መከራውንም ከመሠቀቅ የተነሣ ለመኾኑ አያጠያይቅም። ፍላጎታቸው፡ የእግዚአብሔርን መንግሥት ከመቀበል ይልቅ፡ ለዓለሙ ተገዢ የኾነውን አኗኗራቸውን መምረጡ የሚበልጥ መስሎ ስለታያቸው መኾኑ፡ በዚሁ አድራጎታቸው አረጋግጠውታል።

ያን ከመሰለው የአስተሳሰባቸው አቋም ጋር፡ መምህራችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ የሰው ኹሉ መዳኛ የኾነውን፡ ቅዱስ ሥጋውን መብላትና ክቡር ደሙንም መጠጣት የሚያስፈልጋቸው መኾኑን በነገራቸው ጊዜ፡ ‹ዕፁብ ዝንቱ ነገር፤ ወመኑ ይክል ሰሚዖቶ!?› ማለትም፡ ‹ይህ ነገር ጭንቅ ነው፤ ማንስ ሊሰማው ይችላል?› እያሉ፡ እርሱን መከተልን እንደተዉ ይታወሳል።

እርሱም፡ በየጉባኤያቱ፡ ድርጊታቸውን እየተመለከተ፡ ‹እፎ ዕፁብ ለእለ ቦሙ ንዋይ፡ በዊእ ውስተ መንግሥተ እግዚአብሔር?!› ማለትም፡ ‹ገንዘብ ላላቸው፡ ወደእግዚአብሔር መንግሥት መግባት እንዴት ጭንቅ ነው?!› ይላቸው እንደነበረ፡ በየጊዜው ይዘከራል።

እነዚህና እነርሱን የመሰሉት ጥቅሶች፡ ከዚያ፡ የሚለያይ ሰይፍ ከኾነው፡ ከላይ ከተጠቀሰው፡ ከመለኮታዊው መሪያችን መመሪያ ቃል ጋር፡ የቱን ያህል የተያያዘና ቀጥተኛ የኾነ አግባብነት እንዳላቸው ለመገንዘብ፡ ለማነኛችንም የሚሣነን አይኾንም። (ዮሐ. ፮፥ ፷-፷፮። ሉቃ. ፲፰፤ ፳፬።)

የኋላ ኋላም፡ ይኸው መሪያችን፡ ጨክነው እርሱን ለተከተሉት፡ ‹ተኀየሉ! ትባኡ፡ እንተ ጸባብ አንቀጽ! እብለክሙ፡- 'ብዙኃን እለ የኀሥሡ ይባኡ፤ ወኢይክሉ! ...ወይከውኑ ደኃርት፡ ቅድመ፤ ወቀደምት፡ ይከውኑ ድኅረ።' ማለትም፡ ‹በጠባቡ ደጃፍ ትገቡ ዘንድ፡ ተጋደሉ! እላችኋለሁና፤ ብዙዎች፡ ወደዚያ ሊገቡ ይሻሉ፤ ነገር ግን አይችሉም። ...ኋለኞች፡ ፊተኞች ይኾናሉ፤ ፊተኞችም፡ ኋለኞች ይኾናሉ።' ሲል የተናገራቸው፡ እንዲያው፡ ዝም ብሎ፡ ያለምክንያት አልነበረም፤ አምነው ከተከተሉት፡ ደቀ መዛሙርቱ መካከል፡ <u>የብዙዎቹን</u> መዳከምና ወደኋላ መቅረት፥ ጨርሰውም እስከመለየት መድረሳቸውን ስለተመለከተ ነበር እንጂ።

ይህንም እውነታ፡ ‹ወበእንተ ዝንቱ፡ ብዙኃን እምአርዳኢሁ፡ እለ ገብኡ ድኅሬሆሙ፤ ወኢሖሩ እንከ ምስሌሁ። ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ፡ ለዐሥርቱ ወክልኤቱ፡- 'አንትሙኑ ትፈቅዱኑ ትሑሩ!?'

ማለትም፡ ‹ስለዚህም ነገር፡ ከደቀ መዛሙርቱ መካከል፡ ብዙዎች፡ ወደኋላቸው ተመለሱ፤ ከዚያ ወዲያም፡ ከእርሱ ጋር አልኼዱም። በዚህ ጊዜ፡ ጌታችን ኢየሱስ፡ ለዐሥራ ኹለቱ ሐዋርያት፡- 'እናንተም፡ እንደነርሱ ልትኼዱ ትፈልጋላችሁን?' አላቸው።' የሚለው የመጽሓፍ ቃል ያጸናዋል።

ፈታኙ የክፋት ኃይል፡ ከመጀመሪያዎቹ ሰዎች፡ ከአዳምና ከሔዋን አንሥቶ እስካኹኑ ዘመን ድረስ የቀጠለበትን፡ ወንዶችንም፣ ሴቶችንም፡ ድል ሲያደርግበት የኖረውን፡ ጥበባዊ ወጥመዱን፡ የመዘርጋት ዘመቻውን፡ እኒህን በመሰሉት ደካሞች፥ ብርቱዎች በኾኑትም ላይ ጭምር፡ እንዲህ፡ ሲያካኼድ እንደኖረ፥ ዛሬም እያካኼደ መኾኑን፡ የቅዱሱ ኪዳን ልጆች ኹሉ ያውቁታል።

ይኸውም፡ ሰብኣዊት ነፍስ፡ በአንድ በኩል፡ ለሥጋዋ ማሳሳቻ በሚኾነው፡ በግዙፉ የመብልና የገንዘብ ስስት፥ በሌላው በኩል ደግሞ፡ ለመንፈሷ ማሰናከያ በኾነው፡ በረቂቁ የክብርና የሥልጣን ጉጉት፡ ሰዎች ኹሉ፡ እንዴት ሊሸነፉ እንደሚችሉ፡ ዘዴውንና ብልሃቱን አረጋግጦ፡ ይህንኑ፡ በተግባር እየተጠቀመበት፡ እንዴት፡ ወደርሱ ጎራ እንደሚሰበስባቸው ነው።

ከዚሁ የክፋት ኃይል፡ በቅድሚያ የቀረበባትን ፈተና፡ ተቋቍማና አሸንፋ፡ የእግዚአብሔር እናት ለመኾን ከበቃችው፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ፡ ሰው በኾነው አምላክ፡ በራሱ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ሳይቀር፡ ዲያብሎስ፡ ይህን፡ ፈታኝ የኾነውን የክፋት ኃይሉን ወጥመድ፡ በድፍረት ዘርግቶ፡ የትስብእቱን ታላቅ ዓላማ ለማሳሳትና ለማሰናከል ከመሞከር ወደኋላ አላለም፤ ነገር ግን፡ ያው እንደሚታወቀው፡ ዲያብሎስ፡ ከነኃይሉ፡ በምን ዓይነቱ መለኮታዊ የትሕትና እሳት ተደምስሶና የትዕግሥት ማዕበል ተጥለቅልቆ፡ በዘለዓለም ድል እንደተመታ፡ የገዳመ ቆሮንቶስና የጌቴሴማኒ የገድል ምሥራች ድርሳናት ሲያውጁት ይኖራሉ።

ታዲያ! እኛ የዛሬዎቹ ኪዳናውያንና ኪዳናውያት የኢትዮጵያ ልጆች፡ በእውነት፡ የቅዱሱ ኪዳን ታማኞች ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት መኾናችንን፡ ለየራሳችንና ለእግዚአብሔር፥ ለሰዎችም አረጋግጠን የምናሳየው፥ የምንመሰክረውስ እንዴት ሊኾን ነው?

መሪያችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ "አምነንብሃል!" ብለው፡ በተከተሉት ደቀ መዛሙርቱ መካከል ሳይቀር፡ እየተሻኼደ ያለውን፡ አሳፋሪ ኹኔታ አይቶ፡ ለሓዋርያቱ ያቀረበላቸውን፡ ያንኑ ጥያቄ፡ ዛሬም እኮ፡ እንኳንስ፡ ፍጡራን፡ በገሃድ የሚመለከቱትን፡ ግዙፉን ቀርቶ፡ በየልቦናችን ውስጥ የሚናወጠውን ረቂቁን፡ የሃይማኖት ማዕበል ጭምር፡ በመንፈስ ቅዱስ ስለሚያውቀው፡ ለእያንዳንዳችን፡ በየጊዜው ያቀርበዋል።

ታዲያ! እውነተኞቹ የኢትዮጵያ ልጆች የመኾናችንን ማስረጃ፡ በቅዱሱ ኪዳን ማኅተም ያረጋገጥነው፡ እኛ፡ ኪዳናውያንና ኪዳናውያት፡ በእያንዳንዳችን በኩል፡ የምንሰጠው መልስ፡ የትኛው ሊኾን ነው?

እንደቅዱሳን ሓዋርያቱ፡ ‹እግዚኦ! ኀበ መኑ ነሓውር፡ እንዘ ቃለ ሕይወት ዘለዓለም ብከ? ወንሕነሰ፡ አመንነ፤ ወአእመርነ፡ ከመ አንተ ውእቱ ክርስቶስ፥ ወልዱ ለእግዚአብሔር ሕያው።" ማለትም፡ ‹አቤቱ! የዘለዓለም ሕይወት የሚገኘበት ቃል፡ ባለቤት የኾንኸው፡ አንተ እያለህ፡ ወደሌላ፡ ወደማን እንኼዳለን? እኛማ፡ የሕያው እግዚአብሔር፡ ልጁ፡ አንተ፡ መሢሑ እንደኾንህ፡ አውቀናል፤ አምነንማል።› የሚለውን ነውን? (ዮሓ. ፮፥ ፷፰-፷፱።)

ወይስ፡ ከእርሱ፡ ከመምህራቸው ተለይተው፡ ወደኋላቸው የተመለሱት፡ እኒያ፡ ቃላቸው፡ ከላይ የተገለጸውን፡ የሌሎቹን?

እኛማ፡ እንደቀደሙት ታማኞቹ፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ በፈጣሪያችንና በቅድስት እናቱ መንበር ፊት የተፈጠምንበትን፡ የቃል ኪዳን ምስክርነታችንን በማጽደቅ፡ ያው፡ ጥቅሱ፡ ቀደም ብሎ ተጽፎ እንደተነበበው፡ በአዲስ ኪዳኑ የተሰጠውን፥ ለአብርሃምና ለሣራም ቀርቦላቸው፡ ለፍሬያማው ምግባር ያበቁትን፡ የብሉይ ኪዳኑን የሰይፍ መለኮታዊ ቃል የሚመስለውን፡ የፈተናና የመከራ ዓይነት፡ በፍጹም ፈቃደኛነትና ትዕግሥት፥ ቆራጥነትና ጽናት ተቀብለን፥ እንደሓዋርያት፡ በተግባር ላይ የምናውለው እንኾናለን።

የዚህንም ምግባር አርአያነት፡ ከአብርሃምና ከሣራ ብቻ ሳይኾን፡ ከእነርሱ ከቀደሙትና እነርሱን ከተከተሉት፡ ከሰባቱ ቃል ኪዳናት ተዋዋዮች፡ ከአዳምና ሔዋን፥ ከኖኅና ሐይከል፥ ከመልከ-ጼዴቅና ኢየሩሳሌም፥ ከሙሴና ሲጳራ፥ ከዳዊትና ቤትሳባ፥ በመጨረሻም፡ በድንግል ማርያምና በልጇ ኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ከደረሰው የፈተናና የመከራ ጽዋ፡ የተገኘውን አንጸባራቂ የድል ዘውድ፡ በሰንደቅ ዓላማችን ላይ አሥፍረንና ከፊታችን እያበራ እንዲመራን አንግበን፡ ዘለዓለማዊ የኾነውን፡ የነጻነት ህልውናችንን እንቀጥላለን።

እንግዴህ፡ እጅግ ብዙዎች የኾኑትን፡ የሌሎቹን ኪዳናውያትና ኪዳናውያን ገድል፡ ለወደፊቱ የዝክረ ነገር አቅርቦታችን አቆይቼ፡ እኔ፡ ንቡረ-እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ-ኢየሱስ፡ ይህ መልእክት፡ ወደእናንተ ይደርስ ዘንድ፡ በዚህ መልኩና ይዘቱ፡ እንዲህ አድርጌ ልጽፍላችሁ የተነሣሁበትን መነሻ ምክንያት፡ እዚህ ላይ፡ ባጭሩ እገልጽላችሁ ዘንድ፡ ፍቀዱልኝ!

እርሱም፡ እንዲህ ነው፡- <u>"የሚለያይ ሰይፍ"</u> የተባለውንና ከላይ የተጠቀሰውን፡ የአዲስ ኪዳኑን መለኮታዊ መመሪያ ቃል በሚመለከት፡ በብዙዎቻችሁ ላይ፡ ከየቤተሰባችሁ እየደረሰ ያለውን ፈተናና መከራ አየሁ፤ ከዚህ የተነሣም፡ ይኸው ጽዋ፡ በኹላችሁም ላይ ሊደርስ እንደሚችል ተገነዘብሁ።

እነሆ፡ ይህ ግንዛቤዬ ደግሞ፡ በውስጤ፡ አንድ ጥያቄን እንዲቀሰቀስ አደረገ። ያም፡ "ባለቤቴ፡ ኪዳናዊት እመቤት ራሔል ዘካርያስና እኔ፥ ከልጆቻችን ጋር ዐብረን፡ ይህንኑ፡ የፈተና እሳትና የመከራ ማዕበል፡ በቅዱሱ ኪዳን ጸጋና በረከት፡ ተቋቁመነው፡ ይኸው፡ እያሳለፍነው ስለምንገኝ፡ ታዲያ! በዚህ ረገድ የደረሰብንን ልምዳችንን፡ በአብነት ያገለግል ዘንድ፡ በይፋ አውጥተነው፡ ለምን፡ እኛን ለመሰሉት ኹሉ፡ ለምንባብ አናበቃውም?" የሚል ነበር።

ጥያቄው፡ ተፈጻሚነትን ካገኘም፡ ይህንኑ የፈተና እሳትና የመከራ ማዕበል፡ እኛ፡ እስካኹን፡ እንዴት አድርገን ተቋቁመን ልናሳልፈው እንደቻልን፥ አኹንም፡ በምን ዓይነት ይዘት እያስተናገድነው እንዳለን፡ በደብዳቤ ልውውጥ በተዘገበ ዝርዝር ሓተታ የተደገፈ ስለኾነ፡ በምሳሌነቱ እንደሚጠቅም አመንንበት።

ይህ ጥያቄ፡ እንደምትመለከቱት፡ ለራሱ ለጥያቄው፡ መልስ የኾነውን መፍትሔ ጭምር ይዞልን ስለመጣ፡ ይህን መልእክት አዘጋጅቶ፡ ለእናንተ የማቅረቡ ግዳጅ፡ በእኛ ዘንድ፡ አስፈላጊ ኾነ።

እንግዴህ፡ እናንተ፡ የዛሬዎቹ ኪዳናውያንና ኪዳናውያት በበቃችሁበት፥ የወደፊቶቹም በምትደርሱበት፡ በዚሁ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖታችሁና ምግባራችሁ ጸንታችሁ ትቀጥሉበት ዘንድ፥ ከያግጣጫው የሚገጥማችሁንም ማናቸውንም ዓይነት ፈተናና መከራ ተቋቍማችሁ ታሸንፉበት ዘንድ፥ ትምህርትና አብነት ኾኖ ያገለግላችሁም ዘንድ፡ ይህን ገጸ በረከት አቅርበንላችኋልና፡ የኹለንተና ትጥቃችሁን፡ በእውነትና በመንፈስ ቅዱስ አምልኳችሁ አሚልታችሁና አጠናቅቃችሁ ተመልከቱት! ተጠቀሙበትም!

\+ \+ \+